

# ሚሲዮናዊ የህይወት ታሪክ

## ኤሪክ ሄነሪ ሊዴል
## የትውልድ ዘመን : 1902 - 1945
## የትውልድ ቦታ: ቻይና

ኤሪክ ሄንሪ ልዴል የተወለደው ቻይና ውስጥ ከስኮትላንዳዊ ሚስዮናውያን ቤተሰብ ነበር። ለትምህርት ኤልተም ኮሌጅ፣ ለንደን ያቀና ሲሆን፣ በስኮትላንድ ኤድንበርግ ዩኒቨርሲቲም ትምህርቱን ተከታትሎ ተመርቋል። በዚያም ድንቅ ስፖርተኛ እና በስኮትላንድ ውስጥ ፈጣኑ ሯጭ መሆን ችሎ ነበር። እ.ኤ.አ. በ1924 በፓሪስ በተካሄደው የኦሎምፒክ የ100 ሜትር ውድድር እንግሊዝን ወክሎ ለመወዳደር ሲመረጥ መርሃ ግብሩ እሁድ በመሆኑ ወደ ውድድሩ ለመግባት ፈቃደኛ ሳይሆን ቀርቷል። ለእርሱ እሑድ ማለት ለእግዚአብሔር የተለየና ቅዱስ ቀን ነበር። ነገር ግን በቂ ዝግጅት ባላደረገበት የ400 ሜትር ውድድር የወርቅ ሜዳሊያ አስገኝቷል። በእርግጥም እግዚአብሔር የሚያከብሩትን ያከብራል።

ሊዴል ስኬቱን ስለወንጌልን ለማካፈል እና ብዙ ወጣቶችን ወደ ክርስቶስ ብርሃን ለማምጣት እንደ እድል ተጠቅሞበታል። ወጣት እና ትሑቱ ክርስቲያን አትሌት ምንም እንኳን በጉልምስና ዕድሜው የነበረ ቢሆንም፣ ከከበረ ሥራው ወጥቶ የወላጆቹን ፈለግ በመከተል በቻይና ሚስዮናዊ ሆኗል። ወደ ቻይና ከመሄዱ በፊት በኤድንበርግ በሚገኘው የስኮትላንድ ጉባኤ ኮሌጅ ትምህርት ወስዷል።

እ.ኤ.አ. በ 1925 ቻይና ከደረሰ በኋላ በቲየንሲን በሚገኘው አንግሎ-ቻይኒዝ ክርስቲያን ኮሌጅ ሳይንስ ፣ እንግሊዝኛ እና ስፖርት አስተምሯል። በክርስትና መርህ የታነጸ እና የምዕራባውያንን ሳይንስ ያጠና የተማረ ትውልድ በማስነሳት ሀገሪቱን እንደሚለውጥ ያምን ነበር። እ.ኤ.አ. በ1941 የጃፓን ጦር ቻይናን በወረረ ጊዜ የብሪታንያ ዜጎች አገሪቱን ለቀው እንዲወጡ ታዘዙ፤ ይሁን እንጂ ሊዴል ቤተሰቡን በመላክ ወደ ኋላ ቀርቷል። ይህም በጃፓን ወታደሮች ለመያዙ ምክኒያት ነበር። ምንም እንኳን ከባድ ሁኔታና የምግብ እጥረት ቢያጋጥመውም ቻይናውያንን ለማገልገል በእግርና በብስክሌት ተጓዘ። በእስረኞች ልውውጥ ፕሮግራም ከቻይና የመውጣት እድል ቢያገኝም ቦታውን ለሌላ ነፍሰ ጡር ሴት በመስጠት በዚያ ቀረ፤ ቀሪውን ህይወቱን በጦርነት ካምፖች ውስጥ የእሁድ አገልግሎቶችን በመስጠት በማስተማር አሳልፏል። በከባድ የተመጣጠነ ምግብ እጦት የተዳከመው ሊዴል በ1945 ከፈጣሪው ጋር በገነት ለመኖር የዚህን ዓለም ጦርነቶች ትቶ አልፏል።

የተወደድክ ፣ ለአንተ የበለጠ አስፈላጊ የሆነው ምንድነው? ክርስቲያናዊ ማንነት ወይስ ዓለማዊ ስኬት?
ጌታ ሆይ፣ የእምነትን ሩጫ እንደ ሊንደል ፅናት እና ድፍረት እንድሮጥ እርዳኝ፣ አሜን!

እጣሪ፡- ዶክተር ሄፕሲባህ ሴልቫም